በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 238782
ታህሳስ 24 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም የደቡብ ሪጅን
ተጠሪ፡- መኩሪያ ባሳዬ አስመጪና ላኪ ድርጅት
መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወጪና ኪሳራ ጋር በተያያዘ የጠበቃ አበል ክፍያ አወሳሰን ስርዓት የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአመልካች ቅሬታ ነጥብ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ሲወስን ተጠሪ ከጠበቃቸው ጋር ያደረጉት ውል መሰረት አድርገው ብር 10000(አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ የክስ ግምት ከሆነው ብር 149120.20 ሳንቲም ላይ ከ10% በላይ ሊወሰን የማገባ ሆኖ እያለ በቁርጥ ብር 50000(ሀምሳ ሺህ ብር) እንድከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በሚል በሰበር እንዲታረም የቀረበ አቤቱታ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን አመልካች ተከሳሽ በእንዲሁም በዚህ ክርክር ያልተካተቱ አቶ አንተነህ ክንፍዬ የተባሉ ጣልቃገብ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ መዝገቡ እንደሚያሳየዉ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ይዘቱ ሲታይ፡- አመልካች የቴሌኮም ኔትወርክ ማቀባበያ ሳጥኑ የተጠሪ ድርጅት የሆነው የሆቴሉ መግቢያና መውቻ በር የዘጋ መሆኑን አምኖ የተከለው ሳጥን ለማንሳት ተስማምቶ የማንሻ ወጪ ብር 149120.20 በደረሰኝ ቁጥር 8984080 ካስከፈለን በኃላ ሳጥኑን ከቦታው ባለማንሳቱ የተጠሪን ድርጅት ቤት መግቢያና መውጫ እየዘጋ መቀጠሉ የሁከት ተግባር በመሆኑ ይህ የአሁኑ አመልካች የሁከት ተግባር ተወግዶ የአሁኑ አመልካች የተከለው ኮንቴነር በተጠሪ ይዞታ በስተቀኝ በኩል አንስቶ እንዲተክል እንዲወሰንልኝ እንዲሁም በክርክር ምክንያት ያወጣሁት ወጪና ኪሳራ እንዲተካልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ አከራክሮ የአሁኑ አመልካች የኔትወርክ ማቀባበያ ኮንትኔር አሁን ከተተከለበት አንስቶ የሀዋሳ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በ05/11/2013ዓ.ም በቁጥር 341/322 በሰጠው ማረጋገጫ መሰረት የአሁኑ ተጠሪ ሆቴል አገልግሎት እና ስር ጣልቃገብ ህንጻ አመቺነትን በማይከለክል ሁኔታ አንስቶ በአሁኑ ተጠሪ ሆቴል ፊት ለፊት ወዳለው የህዝብ ክፍት ቦታ ሊያነሳ ይገባል በሚል ሲወስን የአሁኑ ተጠሪ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ በመ/ቁ 31461፤ በቀን 17/10/2014ዓ.ም የወሰነ ሲሆን ይህ ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03808፤ በቀን 30/3/2015ዓ.ም ተቀብሎ ያፀናው ሲሆን አሁኑ አመልካች ተረቺ፤ የአሁኑ ተጠሪ ረቺ ሆነው ክርክሩ መጠናቀቁን ያሳያል፡፡ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የወጪ ዝርዝር በማቅረብ አመልካችን መጠየቅ እንደሚችሉ በጠበቀላቸው መብት መሰረት ተጠሪ በክርክሩ ምክንያት ያወጡት ወጭ በአመልካች እንዲተካላቸው ከጠየቁት ዳኝነት ውስጥ ለጠበቃ የተከፈለ ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

በአሁኑ አመልካች በኩል የጠበቃ አበል ሲወሰን የጉዳዩ ውስብስብነት እና የጥብቅና አገልግሎት ከተሰጠበት አገልግሎት መጠን አንጻር ሲወሰን የክርክሩ ግምት ሚዛናዊ የሆነ ክፍያ ለመወሰን እንደመስፈርት ሊወሰድ እንደሚገባና የሚወሰነውም የክርክሩ ግምት ከሆነው ወይም በዳኝነት ከተወሰነው 10% ሊበልጥ እንደማይገባ በሰ/መ/ቁ 105765 የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ጠቅሶ በዚሁ ጉዳይ የክርክር ግምቱ 149120.40(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሀያ ብር ከአርባ ሳንቲም) ብቻ በመሆኑ በዚህ ብር መጠን ለጠበቃ አበል መክፈል ካለብኝ የክርክር ግምት ከሆነው ገንዘብ መጠን ላይ 10% ሲሰላ ከብር 14912.04(አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከአራት ሳንቲም) ሊበልጥ አይገባም በሚል ተከራክረዋል፡፡

የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የጠበቃ አበል በቁርጥ ብር 50,000(ሀምሳ ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት በመ/ቁ 31461፤ በቀን 6/12/2014ዓ.ም ወስኗል፡፡

አመልካች ይግባኝ ቅሬታቸዉን ለሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 04235 ያቀረቡ ቢሆንም በቀን 30/03/2015 በዋለዉ የአመልካች ይግባኝ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ላይ ሲሆን ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ንብረት ግምት 149,120.40(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሀያ ብር ከአርባ ሳንቲም) ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ከ10% በላይ ከፍ አድርጎ የጠበቃ አበል ወጭውን በተመለከተ ብር 50,000(ሀምሳ ሺህ ብር) የወሰነበትን አግባብነት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 105765 በሰጠው የህግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ተጠሪ ጥር 08 ቀን 2015ዓ.ም ጽፈው የሰጡት መልስ ባጭሩ፡- ክሴ ለጊዜው በገንዘብ ሊተመን የማይችለውን የሆቴል ድርጅት የመግቢያና መውጫ መብት ለማስከበር የቀረበ እንጂ የድርጅቱ ግምት በመጥቀስ አልያም በአመልካች ድርጊት የተነሳ በድርጅቴ መግቢያ መውጫ በመዘጋቱ ከንግድ ስራዬ ላገኝ ስችል ያጣሁትን ኪሳራ ለማስከፈል ያቀረብኩት ክስ ስላልሆነ በክሴ የጠቀስኩት ገንዘብ መጠን ሳጥኑ ለማስነሳት ለአመልካች የከፈልኩት ገንዘብ መጠን በመሆኑ የሚያከራክረው ሀብት ግምት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል እንዳልሆነ፤ በአመልካች ከቅንልቦና ውጭ በመከራከሩ ምክንያት ክርክሩም ረዥርም ጊዜ የፈጀ እንደሆነ፤ከጠበቃ ጋር ያደረጉት ውል ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) ሆኖ እያለ ብር 50,000 ብቻ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍለኝ መወሰኑ ተጠሪን የሚጎዳ እንጂ የስር ውሳኔው አመልካችን ሊጎዳ ስለማይችል በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ሊፀና ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር እንዲቀርብ የተያዘው ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በዋናዉ ክስ የአሁኑ አመልካች ተረቺ፤ ተጠሪ ተረቺ መሆናቸዉና ክሱ ያስከተለዉን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር በማቅረብ እንዲጠይቁ ለተጠሪ የተወሰነ መሆኑም አላከራከረም፡፡ የአመልካች ቅሬታ ነጥብ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት ግምት 149120.40(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሀያ ብር ከአርባ ሳንቲም) ሆኖ እያለ የጠበቃ አበል ለመወሰን የክርክር ግምት መሰረት ማድረግ እንደሚገባና የክርክር ግምት ከሆነው ወይም ከተወሰነው ላይ 10% በላይ ሊወሰን እንደማይገባ በሰ/መ/ቁ 105765 የተሰጠው የህግ ትርጉም በሚቃረን ሁኔታ የክርክር ግምት ከሆነው 10% ሲሰላ ከብር 14,912.04 (አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከአራት ሳንቲም) በላይ ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ ሳይኖር ስር ፍርድ ቤት በቁርጥ ብር 50,000(ሀምሳ ሺህ) ለተጠሪው እንድከፍል መወሰኑ ተገቢ አደለም በሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች በሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 463 ድንጋጌ መሰረት የጠበቃ አበልን ጨምሮ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር በቀረበላቸው ጊዜ የወጭውንና ኪሳራውን ልክ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 464 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት አድርገው መወሰን የሚችሉ ሲሆን የድንጋጌው ይዘት ወጪና ኪሳራ ዓይነቱን የመለየት እና መጠኑን የመቀነስ ስልጣን ለፍርድ ቤቱ የተተወ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወጭና ኪሳራ ዝርዝር ሲያቀርቡ ጠበቃ አበል ከጠበቃቸው ጋር ያደረጉት ውል ሰነድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማስረጃነት በማያያዝ ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ተጠሪ እንዲከፈላቸው ከጠየቁት ክፍያ መጠን በመቀነስ በቁርጥ ብር 50,000(ሀምሳ ሺህ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የጠበቃ አበል መጠንን አስመልክቶ በቁርጥ የመወሰኑን አግባብት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ እንደሚታወቀው የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመወሰን በልምድ ከዳበረው እና በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው የአከፋል መርህ ጉዳዩ የወሰደው ጊዜ፣የሚጠይቀው ድካም፣ የጉዳዩ ውስብስብነት፤የክርክሩ ግምት ታሳቢ የሚደረጉ ሲሆኑ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ሥራውን ያለውን ውጣ ውረድ ድካምና ያስከተለው ወጭ ታሳቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ያለምንም ገደብ ስምምነት የሚደረግበት አለመሆኑ ከስነስርኣት ህጉ የምንገነዘበው ነው፡፡ በተጨማሪም የጥብቅና አገልግሎት ዋጋ ክፍያ ፍትሀዊና ሚዛናዊ ሊሆን እንደሚገባና ተገቢ የሆነውን የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የተደረገው ጥረት (ድካም)፣የወሰደው ጊዜ እና የጉዳዩ ውስብስብነት ታሳቢ ማድረጉ ሚዛናዊ የሆነ ክፍያ ለመወሰን እንደ አንድ መስፈርት የሚወሰድ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 105767 የሕግ ትርጉም ሰትቶበታል፡፡ ለጥብቅና ሙያ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የሚያገለግሉ መመዘኛዎች በሚመለከትም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 42 ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የጠበቃ አበል መጠንን ለመወሰን ጠበቃው የሰጠውን አገልግሎት፣ የወሰደውን ጊዜና የጠየቀውን ድካም፣ የጉዳዩን አዲስነትና አስቸጋሪነት፣ ተመሳሳይ ጉዳዮች በተለምዶ የሚያስከፍሉትን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠን፣ የክርክሩ መነሻ የሆነው ሃብት ግምት፣የሚያስገኘው ውጤት እና መሰል ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

እንዲሁም የጠበቃ አበል ወጭን ለማስረዳት በጠበቃው እና በደንበኛው መካከል የተደረገው ውል እንደማንኛውም ወጭን ለማስረዳት እንደሚቀርብ ማስረጃ የሚታይ እንጂ የጥብቅና አገልግሎት ውል ክፍያ ስምምነት ሰነዱ እንዳለ ተቀባይነት ያለውና አስገዳጅነት ያለው ማስረጃ እንዳልሆነም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 17191፣53462፣60848 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በግራቀኙ መሀከል የነበረው ክርክር አመልካች የተጠሪ ሆቴል ድርጅት የሆነው መውጫ መግቢያ ላይ የኔትወርክ ማቀባበያ ሳጥን በመትከል የፈጠረው ሁከት ተወግዶ በሆቴሉ መውጫ መግቢያ ላይ አመልካች የተከለው ሳጥን እንዲያነሳ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ የክርክር ግምት በሚል የጠቀሱት 149120.40 የገንዘብ መጠን አመልካች የተከለውን የኔትወርክ ማቀባበያ ሳጥን ከቦታው ለማንሳት የሚያስፈልገው ወጭ በሚል ለአመልካች የከፈሉት ክፍያ መጠን መሆኑን በዋናው ክርክር ከተሰጠው ውሳኔ የምንረዳው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በዚህ ሰበር ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ያገኘነው ነጥብ የጠበቃ አበል ሲወሰን በቁርጥ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሲሆን እንደሚታወቀው የጠበቃ አበል ለመወሰን ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት መመዘኛዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰኑ የፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወሰነው መጠን የተጋነነ እንዳይሆን ጥንቃቄ ለማድረግ በቁርጥ እንዲሁ ከመወሰን ይልቅ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ክርክር በቀረበ ጊዜ በፐርሰንት ማስቀመጡ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የፈጀው ጊዜ ሲታይ በዋናው ክርክር ክስ የቀረበው በ17/2/2014ዓ.ም ክስ ቀርቦ በ17/10/2014ዓ.ም ውሳኔ ማግኘቱ ክርክሩ ረዥም ጊዜ ወስዷል ለማለት የማይቻልና ውስብስብነት ያልነበረው ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የጠበቃ አበል ሲወስን ይህን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በፐርሰንት በማስቀመጥ መወሰን ሲችል እንዲሁ በቁርጥ መወሰኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በፐርሰንት ሲወሰን ምን ያህል ሊወሰን ይገባል የሚለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎቱ ስለ ጠበቃ አበል ክፍያ አወሳሰን ስርኣት በሚመለከት የሰጣቸው ውሳኔዎች እንደ ገዢ የህግ ትርጉም ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉት ፍርድ ቤቶች የጠበቃ አበል ክፍያ ሲወስን ሊከተሉት የሚገባው ስርኣት በሚመለከት የተሰጠው የሕግ ትርጉምን እንጂ ከዚህ ውጭ ያለው ፐርሰንቱን በተመለከተ እንደ ጉዳዩ እየታየ የሚወሰን ከሚሆን በስተቀር አመልካች በክርክሩ በጠቀሰው ሰበር መዝገብ ቁጥር 105765 ላይም ሆነ በሌሎች ስለወጭና ኪሳራ አወሳሰን በሚመለከት በተሰጡ የሰበር ውሳኔዎች የጠበቃ አበል 10% በሚል ቢወሰን እንኳ በዛው ጉዳይ የነበረው ክርክር መሰረት አድርጎ ፐርሰንቱ መወሰኑን የሚያሳይ እንጂ በሌሎች ጉዳዮችም ከ10% በላይም ሆነ በታች ሊወሰን አይችልም ማለት አደለም፡፡ በአመልካች በኩል በሰበር መዝገብ ቁጥር 105765 የሰጠው ውሳኔ ጠቅሰው የጠበቃ አበል የክርክር ሀብት ግምት ከሆነው 10% በላይ ሊወሰን አይገባም በሚል የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ጉዳይ በዋናው ጉዳይ የነበረው ክርክር ረዥም ጊዜ ያልወሰደና፤ ጉዳዩም ያልተወሳሰበ ሆኖ እያለ ይህን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የጠበቃ አበል መጠኑ በፐርሰነት በማስቀመጥ መወሰን ሲችል በቁርጥ አመልካች ብር 50,000(ሀምሳ ሺህ) እንዲከፍል በመወሰኑ የተወሰነው የገንዘብ መጠን የተጋነነ እንዲሆን ያደረገው በመሆኑ የክርክር ግምት ከሆነው ሊከፍል የሚገባው በፐርሰንት በማስቀመጥ መጠኑ ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ስለወጭና ኪሳራ አወሳሰን የሚመለከቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 462 እስከ 464 ያሉት ድንጋጌዎች እንዲሁም በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 ስር ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ አተገባበር ስህተት የተፈጸመበትና መሻሻል ያለበት በመሆኑ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሲዳማ ክልል ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31461፤ ነሀሴ 06 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 04235፤ በቀን 30/03/2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርኣት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ለ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ሊከፍል የሚገባው የጠበቃ አበል ክፍያ በቁርጥ የተወሰነው ብር 50000(ሀምሳ ሺህ ብር) ሳይን አመልካች የክርክሩ ሀብት ግምት በሚል በክሳቸው ከጠቀሱት የገንዘብ መጠን 149120.40 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሀያ ብር ከአርባ ሳንቲም) የዚህን በፐርሰንት 15% የሚሆነው ብር 22,368.06(ሀያ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ ከስድስት ሳንቲም) ነው በሚል ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !